# ሽጉጤ ደሜ - የደም ድምፅ !

የዛሬውን አያድርገውና አዲስ አበባ ትንሽ ከተማ ነበረች። አሁንማ በጣም ሰፍታለች። የሕዝቡም ቁጥር ጨምሯል።የሽጉጤ ደሜ ታሪክ ሲፈፀም አሁን ካላት ስፋት ጋር ሲወዳደር የትየለሌ ነው። ከሦስት አስር አመታት በፊት አንዱ ሠፈር የተፈፀመው ሌላው ሠፈር ይሰማ ነበር ።ዛሬማ ምኑ ቅጡ ብሽቅጥቅጡ እንኳን ሌላ ሠፈር የተሠራው የጎረቤትም መርዶ አይሰማም። አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙት ሠፈሮች አንዱ <<ልደታ>> ነው። ሠፈሩ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ጥቅጥቅ ብለው የሚኖሩበት ነው። የሠፈሩ ነዋሪ ችግረኝነቱ ሳይበግረው ተፋቅሮ የሚኖር ሲሆን በደስታም ይሁን በሀዘን የማይለያይ ነበር ።

ይህ አሁን የምተርክላችሁ እውነተኛ ታሪክ የተፈፀመው እዚሁ ልደታ ውስጥ ነው ። የልደታ ክልል በውል ተለይቶ አይታወቅም።መንፈሳዊው የልደታ ክልልና ደርጋዊው የቀበሌ ክልል ልዩነታቸው ሰማይና ምድር ያህል ነበር።ከአሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ አንስቶ እስከ ሰንጋተራ ፣ ከተክልዬ አንስቶ እስከ ጨርቆስ ሁሉም ልደታ ነው።የዛ ሠፈር ሰዎች እንኳን ክርስቲያኑ እስላሙም <<ልደትዬን>> ብሎ ከማለ ውሸት የሚባል አይገኝበትም። የልደታ ልጆች ልደታን እንደ ሁለተኛ እናታቸው ነው የሚቆጥሩዋት።አንዳንዴም ልደትዬን እንዳባት ስም እንጂ እንደ ሃይማኖት መግለጫ ማን ወስዶ?

አወይ የልደታ ትዝታ!!! ስንቱን ነገር ያስታውሳል እባካችሁ ? ባልቻ ሆስፒታል ሳይክል የተማርንበት ቦታ ፣ ዋና ለመማር አቫሲዮኒ መሄድ ፣ እግርኳስ ለመጫወት አሸዋ ሜዳ ፣ ጥምቀት ልደታን ማውጣትና ማስገባት ፣ የግንቦት ልደታ ፣ ተስፋ ኮከብ ፣ ባልቻ አባ ነፍሶ ፣ ቢሪሞ ፣ ቶሎሳ ሰፈር ፣ ፍርድ ቤት ፣ ማሕበረ ሠላም ዕድር ፣ የዕድሩ ለፋፊ ማሙዬ ፣ በጠዋት የዕድር ልፈፋው ፣ ጡ - ጡ - ጡ - የቱልቱላ ጨኸት . . . . . .ዕድሩ ምኑ ቅጡ . . . .

ጡ - ጡ - ጡ . . .<< የወይዘሮ አትጠገብ አያት ሰለሞቱ ቀብሩ ልደታ ውስጥ ሰለሚፈፀም የማሕበረ ሠላም ዕድር አባለት በሞላ እንደትገኙ ። ስም ይጠራል ። የቀረ መቀጮ አለው ። ጡ - ጡ - ጡ . . . >>

ማን እንደ ሞተ ለማወቅ ከእንቅልፍ ተነስቶ ወደ ውጭ መሮጥ ፣

- << አባባ ማሙዬ ማን ሞተ ያሉት ? >>
- <<እዚህ ቢሪሞ ወፍጮው ጋ ያሉት ሴትዮ ።የታወቁ ናቸው። ሁለት ጎረምሳ ልጆች ያሏቸው።ለእሜቴ ንገሩ እናንተ አታውቋቸውም ፡፡ለጌቶችም እንዳትረሱ ንገሩ!!>>ጡ - ጡ - ጡ!

የዕድር ለፋፊው የማሙዬ ድምጽ የሚረሳ አይደለም። የእደር ብርጭቆ ልንወስድ ተልከን ስንሄድ የአባባ ማሙዬ አቆጣጠር የሚያስቀን አይረሳም . . . አስራ ሰባት . . . አስራ ስምንት . . . አስራ ዘጠኝ . . . አስራ አስር ( ካያ ) . . . ልደታ የአባታችንን የአባባ ማሙዬን ነፍስ ትጠብቅልን ። ትዝታው ወዴት ወሰደኝ እባካችሁ ። ልደታ ውስጥ ፅፈው የማይጨርሱት ፣ ተናግረውት የማያልቅ ስንት ታሪክ አለ። ከሁሉም ትዝ የሚለኝ የሽጉጤ ደሜ ታሪክ ነው።

ከቀይ ሽብር በኋላ ሁላችንም በፍርሃት የምንኖርበት ፤ በተለይ ልደታ ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ላይ ተገለው የተጣሉት ወጣቶች ግፍ በልደታ ነዋሪዎች ውስጥ ትልቅ ሀዘን ትቶ ያለፈበት፤ ገና የቀይ ሽብር ድንጋጤ ያለቀቀው የልደታ ነዋሪ አምላክ ለዚህ ሁሉ ጉድ መፍረዱ አይቀርም ብሎ እየፀለየ በትዕግስት የሚጠብቅበት፤ ልደታ ይህን ንቀት ያደረሰባትን መንግሥት ልኩን ታሳያዋለች የሚል እምነት በሕዝቡ ውስጥ ሰፍኖ የነበረበት ወቅት ነበር።ምን ያድርግ ? ያ ደሃ ነበር ሕዝብ ከልደታ በስተቀር ምን መተማመኛ አለውና።

የልደታ ሰው የልደታን ተዐምር ይጠብቃል። በግፈኞቹ ላይ የሚደርሰው ሁሉ የልደታ ፍርድ መሆኑን

የሚጠራጠር የለም።ለምሳሌ ያህል ለማ የቀበሌ 02 ሊቀመንበርና  ከሰተ የቀበሌ 07 ሊቀ መንበር ከሙቶ አለቃ ደስታ  የከፍተኛ 22 ሊቀመንበር ጋር ተጣሉ ሲባል <<ገና ልደታ ታባላቸዋለች>>ተባለ።

በመኢሶንና በሰደድ ድርጅቶች መካከል የተነሳውን ጠብ ለማለት ነው።ጋምብለር የአብዮት ጥበቃው ታመመ ሰውነቱ ቆሰለ ተብሎ ሲወራ ደግሞ፣ <<ልደታ በዚህ ይብቃህ ትበለው እሱ እንኳ ምስኪን ነበር>> ብሏል። ጋምብለር የሰፈሩ ኩሊ የነበረ ሲሆን በኋላ አብዮት ጥበቃ የሆነ ነው። መምህር ሙሉጌታ ስልቡ ጤናም የለው ሲባል ደግሞ<< ልደታ በስንት በኩል ትቅጣው ምሕረቱን ትላክለት>> በመባል ታልፏል።እንደ ሁኔታው እየታየ የረገማቸው ሕዝብ መልሶ ምሕረትን ከልደታ ይጠይቃል።

ትንሳዬ የአንበሳ አውቶቡሳ ካድሬ የነበረችው  ተጎሳቆለች ሲባል ደግሞ <<የሰው ደም ገና የሚያደርገውን ታዩታላችሁ ! ልደትዬ የለችማ !>> ተብሎ ወደ ሰማይ እንባ ይረጫል።ይግረም ፖሊሱ ወደ ጎጃም ተዛውሮ የቶሎሳ ሰፈር ልጅ ያኔ በቀይ ሽብር ታስሮ የነበረ አለቃው ሆኖ ተሾመ፤ የሚለው ወሬ ሲሰማ ደግሞ <<ልደትዬ ፈረደች >>።ለእያንዳንዱ ጩኸት ልደታ የራሷ የሆነውን ልዩ ቅጣት ያዘጋጀች ይመስላል። በልደታ ሠፈር ነዋሪዎች እምነት ።

የልደታ ተዐምር ብዙ ነው ። ልጅ እንዲሰጣት ለለመነ ልጅ ፣ ጤንነት ለለመነ ጤንነት ፣ ትምህርት ያልገባው እንኳ ልደትዬ ትምህርቴን ግለጭልኝ ብሎ ይሳላል። ወዘተ  የአካባቢው ነዋሪ በተለይ ልጆቻቸው የተገደሉባቸውን አሮጊትና ሽማግሌዎች ባየ ቁጥር ለልደታ ፍርዱን እንዳትረሳ ማስታወሱ ግን የልደታ ሠፈር ሰው ሁሉ ፀሎት ነበር።

<<አታውቋቸውም እንዴ የነ አበበ ፣ የነ ውብሸት አባት ናቸው እኮ ፣ ልጆቻቸውን ሁሉ ቢጨርሱባቸው ፣ ሀዘኑ ቢበዛባቸው ብቻቸውን እያወሩ የሚሄዱት ፣ ልደታ ይኼን ነገር ዝም ትይ !! ? አዬ ! >> እያንዳንዱ ነዋሪ ልደታ ፍርዷን እንድትሰጥ ይጠይቃል።የልደታ ሕዝብ በቀይ ሽብር ያየውን ግፍ ልደታ እንድትበቀልለት እየለመነ በፀሎት ላይ ነበር ።

አንድ ቀን ጠዋት የሚጠበቀው ተአምር ደረሰ ። ሠፈሩ ተበጠበጠ። የልደታ ሰው በሙሉ ወደ ሜክሲኮ መሮጥ ያዘ ። ጉድ ጉድ ይባል ጀመር ።ሜክሲኮ አደባባይ አካባቢ መሬቱ መጮኽ ጀመረ ። ወሬው አንድ ጊዜ አካባቢውን አጥለቀለቀው።

- <<ምንድነው የሆነው ?>> ብሎ አንዱ ይጠይቃል።
- <<መሬት መጮኽ  ጀመረች ።>> ይላል ከሜክሲኮ አካባቢ የተመለሰው።
- <<የምን መሬት ?>>
- <<ጠቅላላው ሜክሲኮ አደባባይን ይዞ ፣ ዴ አፍሪክን ይዞ ፣ ወደ ታች ደግሞ እስከ ጥይት ፋብሪካ አካባቢ መሬት ይጮኻል ።>>
- <<ምን እያለ ?>>
- <<ሽጉጤ ደሜ ነኝ እያለ ።>>

ወሬው ከቦታ ቦታ እየተዛመተ እንደ ሰደድ እሳት ተቀጣጠለ። ልደትዬ ፈረደች የሚለው ቃል እየተባዛ ሄደ።ልቅሶ ፊታቸውን ያበለዘው አሮጊቶች ወደ ሜክሲኮ አደባባይ ሲሮጡ እግረ መንገዳቸውን ልደትዬን እየተሳለሙ በአጭሩ ምስጋና አቅርበው አለፉ። የሜክሲኮውን ታዐምር የሰማ አብዮት ጥበቃ ደግሞ ትንግርቱ ሳይሞላ ከእግዜር ቁጣ ይድን ይመስል ቤቱ ገብቶ በሩን ዘግቶ ከእግዜር ሊደበቅ ሮጠ። ሌላው አካባቢ ደግሞ ፤

- <<ልደትዬ ተዐምሯ መች ያልቃል? >>  ይባላል።
- <<ምን ተፈጠረ ደግሞ ?>> ይጠየቃል።
- <<የአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ፖሊሶች ደግም እንፈራለን አሉ>>ይባላል
- <<ምኑን?>>
- <<ጨኸት የሚሰማበት ቦታ ላይ መቆፈር>>።
- <<ለምን?>>
- <<የልደታ ቁጣ ነው ብለው>>።

- <<የቱ ጋ ነው ቦታው ?>>
- <<ምን የተወሰነ ቦታ አለው ፡፡ሁሉም ጋ ይሰማል፡፡በቀይ ሽብር የተሙቱት ወጣቶች ደም በዝናብ ታጥቦ ምድር ውስጥ ገብቶ ነው ይባላል>>
- <<ዴ አፍሪክ ብትሄድ እሱ ነው ፡፡ ሰፈሪያን ብትሄድ ይሰማል፡፡ ሜክሲኮ ጋር ብትሄድ ይሰማል ፡፡ ሁሉም ጋር ብትሄድ ይሰማል፡፡ በተለይ ወደ አስፋልት ጥግ ከመጣህ በደንብ ይሰማል፡፡>>
- <<ምንድነው የሚለው ?>>
- <<ሽጉጤ ደሜ ነኝ ነው የሚለው አሉ ፡፡>>
- <<ምን ሆነህ መሬት ገባህ ሲሉት፡፡ አላውቅም ሞቼ ሊሆን ይችላል፡፡ምንም ነገር አላይም ሁሉም ጨለማ ነው ይላል አሉ፡፡>>
- <<ታዲያ ሽጉጤ ደሜ ሰው ይሆን ይሆናል ፡፡ሳይሞት ሞተ ብለው ቸኩለው የቀበሩት ይሆን ? >> ይጠይቃል በመገረም ፡፡
- <<ለመሆኑ በዛ ስም በቀይ ሽብር የተገደለ አለ እንዴ?>>
- <<ሽጉጤ ደሜ የሚባል በቀይ ሽብር የተገደለ ተፈልጎ ጠፋ፡፡ደግሞ እንኳን ስም ስንት ሰው እንደተገደለ በቅጡ ይታወቃል እንዴ?>> ይላል ሌላው፡፡

- <<ሌላኛው ደግሞ << እስቲ አስቡት እነ ቴወድሮስ በላይነህ (አንጃው) ፣እነ ይግረም ፣ እነ ከስተ ፣ እነ ለማ ፣ እነ ሙቶ አለቃ ደስታ ፣ የገደሉት ፡፡ ከፍተኛ አራትን ተውትና ከፍተኛ ሦስትና ከፍተኛ ሃያ ሁለትን ብቻ አስቡት፡፡ እንኳን መሬት መጭኽ ከላይ ደም አለመዝነቡ ? >>

- ሌላው ደግሞ ይደግፋል፡፡ << ማን ማን እንደተገደለ ይታወቃል ብለህ ነው? ከፍተኛ 3 ቀበሌ 53 ያሉ አብዮተኞች ለመሆኑ የገደሉትን ያውቁታል ? ትንባሆ ሞኖፖል የሚገኘው ቀበሌ 07 ቢሆን በመደዳ አደለም እንዴ ሲገድሉ የነበሩት ?>>

- <<የዛ ሁሉ ሰው ደም ቢጮህ ይገርማል እንዴ? ስንት እናት እኮ ነው እንባውን ወደ ሰማይ የረጨው፡፡ ስንት ሽማግሌ አባቶች እኮ ናቸው ይጦረኛል ያሉትን ልጃቸውን ያጡት ፡፡ አሁን ሁላችንም እግዚኦ ማለት ብቻ ነው፡፡ ለሃጥያን የመጣ ለፃድቃን እንዳይተርፍ >> ይላል የእግዜርን ቁጣ የፈራ፡፡

- << ልደታ እንደነሱ እውር አደለችም ሁሉንም በጅማላ የምትቀጣው፡፡ እንደ ጋምብለር አቆሳስላ ለማኝ አድርጋ ነው የምትገለው፡፡ ልደትዬ የምትሠራውን ታውቃለች>> ብሎ እራሱን ያፅናናል - ሌላኛው በልደታ ፍርድ የሚተማመን ሠፈርተኛ ፡፡

- <<ግን እንደሚወራው ከሆነ ልደታ ጋ የተገደሉት በሽጉጥ ነው ፡፡ ደሜ የሚለው ደግሞ የነእርሱን ደም ነው ይባላል፡፡>> ይላል አንዱ ፡፡

- <<እንዲያውም የታወቁ የሰፈሩ ሽማግሌ ልደታን የሠሩት ንግስት ነገሥታት ዘውዲቱ ጥቁር ለብሰው ሲያለቅሱ በሕልሜ አይቻለሁ ብለዋል፡፡ ድርቅ የገባ ጊዜ እኚሁ ሰውዬ ሚኒሊክ ተክዘው አይተዋቸው ነበር ፡፡ ጉድ ነው መቼም፡፡>> ይላል በሕልም የሚያምነው ደግሞ፡፡

- <<አሁን ታዲያ መንግሥት ምን ሊያደርግ ነው ?>> ሌላ ጥያቄ ይነሳል ፡፡ይህ የምድር ውስጥ ጬኸት የደርግን ቁጣ ቀስቅሶ ያስጨርሰናል ብሎ የፈራው፡፡
- <<አየር ወለዶች ከደብረ ዘይት ሊያሰመጣ ነው ይባላል፡፡ለእንደዚህ ዐይነት ጉዳይ ይጠቅሙኛል ብሎ ደርግ ቀድሞ ያሰለጠናቸው ናቸው ነው የሚባለው፡፡ ካለ መንጌ የሚያዛቸው የለም ፡፡ ኃይለኞች ናቸው፡፡ ጉድጓድ ውስጥ እንዳደገ ውሻ ገና ሰው ሲጠጋቸው ላዩ ላይ ነው የሚሰፍሩት ፡፡ >> ይላል በመደነቅ ፡፡

ልደታ ተጨነቀች ፡፡ ቤተክርስቲያን የሚሄደው ሰው ቁጥር ጨመረ ፡፡ኮምኒዝም አንገዳግዶት የነበረው ሃይማኖተኛ ሁሉ ከተደበቀበት ተዐምረ ማርያሙን ይፈልግ ጀመር ፡፡ የስምንተኛው ሺህ መድረስ ምልክቶች እንደገና ተጠቀሱ፡፡ ፍካሬ ኢየሱስ በእየቤቱ ተነገረ፤

<<ከዚያም ወራት መከራ በኋላ ፀሐይ ይጨልማል ፤ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም ፤ ከዋክንትም ከሰማይ ይወድቃሉ ፤ የሰማዮችም ኃይላት ይናወጣሉ ፤ በዚህም ጊዜ የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል ፤ የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፤ የሰው ልጅንም በታላቅ ኃይላና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል ፤ መላእክቱም በታላቅ የመለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል።>>
ማቴ 24፤29

የሰው ልብ ሁሉ በፍርሃት ተያዘ ።የስምንተኛ ሺህ መድረስ ምልክት የሆነውን የመሬት ዋይ ዋይታ ጀመረ። በሌላ በኩል ደግሞ የግፎች ሁሉ ቁንጮ የሆነው ደርግን ደካማው ሕዝብ ሊፋረደው ስላልቻለ ለአምላኩ ያደረገው ፀሎት ስለተሰማለት ሕዝብ ደስ አለው።

በጉጉት የተጠበቁት አየር ወለዶችም መጥተው ድምፁ ወደሚሰማበት የቆሻሻ ቱቦ መግባት ፈሩ። የደፈሩት አውቶማቲክ መሳሪያቸውን ይዘው ትንሽ አንገታቸውን ካስገቡ በኋላ እንዳይገቡ <<ወደ ውጭ የሚገፋቸው ኃይል >> እንዳለ እየተናገሩ ተመለሱ። ደርግ የእግዜርን ኃይል ለመዋጋት ልደታን በታንክ ከበበ ።

ከሶስተኛው ቀን በኋላ ድምፁ እየደከመ መጣ። ስዎች ቢጮኹም መልስ አጡ ። ተፈጥሮ በቁጥጥር ሥር ሆነች። እግዜር ፈራ ፤ ደርግ አሸነፈ ። የልደታ ነዋሪዎች በተሰፋ መቁረጥ ተከበቡ ። ግን ልደታን ሄደው መሳለም አላቆሙም ። የደርግ ካድሬዎች የእግዜር ኃይል ውሸት መሆኑን አመኑ ። ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሰበኩ ።የፀረ አብዮተኞች ሸብር ነው ብለውም ተመፃደቁ ።

በአራተኛው ቀን ከሜክሲኮ በታች ከሚገኝ የቆሻሻ ማስተላለፊያ ቱቦ ውስጥ ጥቁር የሆነ ቆሻሻ የለበሰ አንድ ሰው ብቅ አለ ።በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች ደንግጠው ሮጡ ። ሰውየው ወደ ሰው ሲጠጋ ሰዉ ይሸሸው ጀመር። ፖሊሶች ተጠሩ ።እነርሱም ሊጠጉት ፈሩ። አየር ወለዶችም ከበቡት ። ግን ማንም ሊጠጋው አልደፈረም ። በሩቅ በድምፅ ማጉያ ፤
<< ማነህ አንተ? ስምህን ተናገር ? ብለው ለፈፉ ።>>

<<ሽጉጤ ደሜ >> ብሎ መለሰ።

ሆኖም ማንም ሊጠጋው አልደፈረም። አየር ወለዶቹ በደረታቸው ጠመንጃቸውን ወድረው መሬት ለመሬት ተስበው ደርሰው ያዙት መሬት ላይ አስተኙት ። የፊጥኝ አሰሩትና በመኪና ጭነውት ሄዱ ።

በሳምንቱ በፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ ላይ፤

<< አዲስ አበባን ያስጨነቀው ሽጉጤ ደሜ ተያዘ የሚል አነበብን። ሰዓት እላፊ ደርሶበት የሚሮጠው ሽጉጤ ደሜ አብዮት ጥበቃዎችን ለመሸስ ሲል ዴ-አፍሪክ አካባቢ ካለው ቱቦ ውስጥ ገብቶ በመደበቅ እስከ ሜክሲኮ ድረስ በቱቦ ውስጥ ከሄደ በኋላ ሰካሩ ሲበርድለት መውጫ አጥቶ ሲጮህ እንደነበርና ሕዝቡን እንደረበሸ አትቶ ተገቢውን ቅጣት እንደሚቀበልና ለጊዜው ግን የአዕምሮ ችግር ሊኖርበት ስለሚችል አማኑኤል ሆስፒታል እንደሚገኝ ጋዜጣው በኩራት ገለፀ። ሽጉጤ ደሜ የሰንጋ ተራ አካባቢ የቀን ሠራተኛ ሲሆን ። ደሞዝ ተቀብሎ ውሻ ገዳይ ከሚባለው ጠጅ ቤት ገብቶ ጠጥቶ በከፍተኛ ደረጃ ሰክሮ እንደነበርም ተፃፈ።

የልደታ ሠፈር ወደ መደበኛውን ኑሮዋ ተመለሰች። ልደታና ሕዝቧ እንደገና ፀሎት ጀመሩ። ከዚያ በኋላ ሽጉጤ ደሜ የት እንደደረሰ አይታወቅም ። ደርግ ግን ከዛ በኋላ አስራ ሦስት አመት ሙሉ የሚገድላቸው ሰዎች ደም ይጮኻል ብሎ ሳይፈራ መግደሉን ቀጠለ።

ሰለኛ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም ! ! !